# እንዲጠራ ትግሉ
# ሊነጋ ሲል ይጨልማል

ነብሮ ከጉለሌ

**"ሊነጋ ሲል ይጨልማል" የሚለው አባባል መልዕክቱ ጠንካራ ነው:: ንጋት ስል የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማለ ሲሆን ጨለማ ደግሞ ወያኔና ተጎንባሾቹንት እንዲወክልልኝ ይሁን:: ባገር ላይ የወረደ መዐት እንደማይቀረፍ ጉዱፍ ለዘላለሙ ተተክሎ አይቀርም:: ተወጥሮና ከሮ መበጣጠሱ አይቀሬ ነው:: በጫንቃችን ላይ የተንሰራፋውን የወያኔ መንግስት ገርስሶ ለመጣል ዘዴውም መላውም ቀላል ነበር:: የተቸገርነው ባስመሳይ ድርጅቶች የማወናበድና ህዝቡን የመከፋፈል ረቂቅ ችሎታቸው ነው:: ጠላቶቻችን ብዙ ናቸው:: በድል ለመወጣት ደግሞ ትግሉ ቀላል ሳይሆን እልህ እስጭራሽ መሆኑን አምነን ችሎታችን በፈቀደው ሁሉ ርብርቦሽ ማድረግ ከኛ ሃቀኛ ኢትዮጵያውያን የሚጠበቅብን ግዴታ ነው::**

**አስምሳይ ተቃዋሚዎች የሕዝቡን ትግል ፈር ሲያስለቅቁት በተደጋጋሚ አስተውለናል:: ለነሱ ወያኔ መሰረታው ጠላታቸው አይደለም:: እንዲያውም ወያኔን ወያኔ ብለን እንዳንጠራው ማስፈራሪያ አይነት ምክር እየመከሩን ይገኛሉ:: ከወያኔ ጋር መስራትም ይቻላል ይሉናል:: ለነዚህ አስመሳዮች ዋነኛው የመታገያ ኢላማቸው ለሕዝብ ነጻነት ከቆሙት ድርጅቶች ጋር ነው:: በዚህ ጎራ ውስጥ ብዙ ጸረ-ሕዝብ ግለሰቦችና ግሳንግስ ድርጅቶች ቢካተቱም ባጠቃላዩ ግን በሁለት የባንዳ ክፍል ልንመድባቸው እንችላለን:: የስም አመዳደቡን የተዋስኩት ከኢሕአፓ ስለሆን በቅድሚያ እውቅናውን በመስጠት ላመሰግናቸው ይገባኛል:: ልክ እንደ ዘመነ-ደርጉ በዘንድሮ የወያኔ ዘመንም <u>ባንዳ ምሁራንን</u> ና <u>ባንዳ ደናቁርቱን</u> እንድናይ ተረግመናል:: ዕውቀት ቢለያያቸውም ሁለቱም የባንዳ ክፍል እንድ የሚያደርጋቸው የህዝቡን ትግል ወገበ ሰባራ በማድረግ የወያኔን ዕድሜ ማራዘማቸው ነው:: እንዱ ካንዱ ይሻላል ማለት "ጅብ ይብላኝ ወይስ እንድበሳ" የሚመስል የማይበጅ ምርቻ ውስጥ መግባት አይነት ነው::**

**እነዚህን ባንዳዎች ቀረብ ብሎ ለመረመራቸው ደግሞ ተጨማሪ መገልጫቸውን ሊያስተውል ይችላል::**
**ጸረ-ወያኔ ግን ጸረ-ኢትዮጵያ አንድነት የሆኑ - AFD**
**የወያኔን ዕውቅና ለማግኘት የሚዳክሩ - የብርቱኳኗ አዲስ ድርጅት**
**አቅጣጫ የጠፋቸውና ሁሉንም ቀማሾች ÷ ከኢሕአፓ የፈረጠጠው አንጃ**
**ታማኝ ተቃዋሚዎች - ፓርላማ ውስጥ ያሉት**
**አስስታዊ ድርጅቶች - የግንቦት 7 ድርጅት ነኝ ባዩ**

**ስለ ሁሉም ብዙ ማለት ይቻላል፤ ሆኖም ግን የጥፋት መንገዳቸው ባብዛኛው ግልጽ በመሆኑ ስለጥቂቶቹ ብቻ ትንሽ ማለት እፈልጋለሁ:: <u>ጸረ-ወያኔ ግን ጸረ-ኢትዮጵያ አንድነት</u> ያልኳቸው ጥሩ መገለጫቸው AFD ነው:: ይህ ጉድ በቅጽበት ብቅ ብሎ በቅጽበት የጠፋ የከፉ ምጻት ነበር:: እንደዛሬው "ሕብረት" አያድርገውና የያኔው ሕብረት ይህን የጥፋት መልዕክተኛ የሆነውን ስብስብ በማጋለጥ የተጫወተው ሚና በታሪክ ልዩ ስፍራ ይኖረዋል:: "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" ለAFD የወያኔ ጠላት የሆነው ሻቢያ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት መሆኑን እንዴት ተሳነው? የዚህ እርቃነ ስጋውን የቀረ ስብስብ ርዝራዦች አሁን ደግሞ ይረግሙት የነበረውን የኢሕአፓ ሁለ-ገብ የትግል ስልት አራማጅ መስለው ብቅ ብለዋል:: ገርና ፖለቲካው ላይ ብዙም ግንዛቤ የሌለው አዳማጭ ሲያገኙ የሁለ-ገብ የትግል ስልቱን በጥናትና በምርምር ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙት እንሱ እንደሆኑም ይዋሹታ:: ሰሚ ዕውነት ቢመስለው አይፈረድበትም ምክንያቱም ባንድ ወቅት መሪያቸው ዶክተር ብርሃኑ ጥናቱን ለማካሄድ ከአሜሪካን ተራራ ባንዱ ውስጥ መመነኑን ነግሮን አልነበርምን?**

በሁለ-ገብ የትግል ስልት ማመን አንድ ነገር ነው። የበለጠው ግን የሚታገሉበት ሁለ-ገብ የትግል ስልት ህዝቡን ከወያኔ ነጻ ለማውጣት እንጂ ለግል ስልጣንና ለዝና አለመሆኑን አስረግጠው ማወቅ መቻሉ ላይ ነው። እነ እንቶኔ ይህን ከልብ ተቀብለው ከሆን እንኳን ወደ ሃቀኛው የትግል ጎዳን በደህና መጣችሁ ልንላቸው ይጠበቅብናል።

የሆነ ሆኖ ግን ትግሉ የሚጠራው (1) ትግሉ በሃገር አንድነትና ለወገን ነጻነት ላይ ያነጣጠረ ከሆነ (2) አስመሳዮችን ከሃቀኞች ነጥሎ የተወጣ ከሆን (3) ለግል ዝናና ሃብትን ለማዳበርና የሃቀኛ ድርጅቶችን ታሪክ በማጥፋት በደም የታጠበውን እጃቸውን በሕዝቡ ትግል ለመታጠብ የሚሞክሩትን እጭበርባሪዎች ነጥለን ማውጣት የቻልን እንደሆን ነው።

ሌላው ዘንድሮኛው ጉግማንጉግ ደግሞ <u>አቅጣጫው የጠፋው ሁሉንም ቀማሽ</u> ያልኩት ነው። ስም የለሽ ነው። የሃቀኛ ድርጅት ስም የሙጥኝ ብሎ ይዟል። ከኢሕአፓ ፈርጥጦ የወጣው አንጃ ነው። “መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ” እንደተባለው መሰሪ ተንኮሉን በስም-ጥሩ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጇ የሆነውን የሃቀኛውን የኢሕአፓን  ስም የሙጥኝ ብሏል። የዚህ አንጃ ደጋፊዎች ገና ድሮ የዛሬ ስድስትና ሰባት አመት ገደማ ኢሕአፓ የሚለውን ስም መለወጥ አለብን ብለውው ውስጥ ለውስጥ  ሲያክቸልችሉ እንደነበር ዛሬ የምናስታውሰው ቅሌታቸው ነው። ያኔ የጠሉትን ስም ዛሬ ለምን የሙጥኝ እንዳሉ ለሰሚ አደናጋሪ ነው። የኢሕአፓ ስም ከምድረ-ገጽ እንዲጠፍ በውል የሚፈልጉት ደርግ (ኢሰፓ)ና ወያኔ ብቻ አይደለም። አንጃውም ሞክሮታል። የሚገርመው ግን ይህ አንጃ እንዴ ስሙን ሲጠላ እንዴ ደግሞ ያለስሙ ልኖር አልችልም ሲሉ መታየቱ ነው።

አገር ቤት ገብተን በሕጋዊ መልክ ለመታገል የልመና ፊርማ እንፈርምና ለወያኔ እንጎንበስ የሚለው ምኞታቸው ሁሌ ይገርመኛል። ሕዝቡን ለማደናገር ካልሆነ በስተቀር የኢሕአፓ መሰረታዊ ትግሉ ያለው ካገርቤት እኮ ነው። ትግሉንም የሚያካሐደው በህቡዕ ነው። ዛሬ ፈርጥጠው የውጡት አንጃዎች ኢሕአፓ ባገርቤት ውስጥ የት የት አንዳለ እንወቀው ሲሉ በስብሰባ ሞግተውን ነበር። እንደሚስጢር አውጣጣቸው በህቡዕ የሚታገሉትን ያገርቤቱን አባሎቻችንን ማንነት አግኝተው ቢሆን ኑሮ ዛሬ ሰንት መርዶ በተቀመጥን ነበር። ሁሉን አፍቃሪው አንጃ ለነስዬና ለሌንጮ ደፋቀና ሲሉ ታይተዋል። በቅርቡ አንድ ወሬ እየነፈሰ ነው። ምናልባትም አዝማሚያቸውን በመረዳት ሊሆን ይችል ይሆናል ወይም በርግጥም ተደርጎ ይሆናል አንጃው ለመለሰ የልመና ደብዳብባቤ አስገብቶ መልሱን በመጠባበቅ ላይ ስለመሆኑ ይወራል። መንገዱን ጨርቅ ባደረገላቸው። አንጃው ኢሕአፓን ማፍረስ ችሎ (የህልም እንጀራ) ቢሆን ኑሮ ለወያኔ የሚያስፈነድቅ እጅ መንሻ ስጦታ በያዘ ነበር።

ሀሻሕአፓ  የሕዝብ የበላይነት እስኪሟላ ድረስ በትግሉ መግፋተኝ እንደሚቀጥልበቱ አስረግጦ መናገር ይቻላል። ይህን የምስክርነት ቃል ለመስጠት የምደፍረው ይህ ሃቀኛ ድርጅት ላለፉት 36 አመታት ያደረገውን መስዋእትነት በመመልከት ነው። በነገራችን ላይ ይህን የኢሕአፓን የዳበረ የትግል ተመክሮ ለማጣጣል የሚያክለቸሉ ግለሰቦችን ቀጭን ድርጅቶች ተመክሮውን ዜሮ ሊያደርጉ ሲፈላሰፉ ማየቱ ያቅለሸልሻል። በቅርቡ አቶ ጽጌ በፓል ቶክ ላይ የለፈለፈውን ወተት አለኝ በሰማይ ተስፍ ሰማሁ። አባባሉን ባጭሩ ላስቀምጠውና አቶ ጽጌ ወያኔን የምናጠፋው በአመታት በተቆጠረ ትግል ሳይሆን በወራት ያውም ባጭር ወራት (አንድ ወር ወይስ ሁለት ወራት?) ነው ብለውናል። ቃለ-መጥይቁን ካስደመጡን ይሆው ወደ ሁለት ወር ሊሆን ነው። ያውም ጎንተል ለማድረግ ፈልገው እንዳንድ ድርጅቶች በዘመናት ታግለው ለስልጣን አልበቁም ብለዋል።ኢሕአፓን ለመንካት። አቶ ጽጌ ሃሳባቸው የጅል ሆነ እንጂ የዘንድሮው የፖለቲካ እድገት ካለፉት ሰላሳ አመታት  በነኢሕአፓና በመሰሉት ሃቀኛ ድርጅቶች ተዋድቆ የተገኘ ነው። እሳቸውም የዚሁ ሂደት ውጤት መሆናቸውን መካድ አይገባቸውም። ሌላው ቢቀር የፖለቲካ ሀ ሁ ያስጎነጫቸውን ኢሕአፓን ማመስገን ቢከብዳቸው ዕውነቱን ግን መካድ አይጠበቅባቸውም። “ያጎረሰ እጅ ነካሽ” እንዲሉ።

ከሰሞኑ ግርግ አንድ በሚቀጥለው ምርጫ ሊሆን እየተሴረበት ያለ ጉዳይ ማንሳት እወዳለሁ:: 2010 ፈጥኖ ይደርሳል:: የሚወዳደረውም የማይወዳደረውም ካሁን ጀምሮ ታውቋል:: ኢሕአፓ ጦረኛ ነው ተብሎ ገና ድሮውኑ በወያኔ ተባሯል:: **መኢአድ** ቀደም ሲል ስሙ ቅንጅት በነበረበት ጊዜ ያቀረበው መስፈርቶች ካልተመለሱ ውድድሩ ውስጥ እንደማይገባ አስታውቋል:: ልወዳደር ነው ቢልም ወያኔ መሰናከል እንደሚፈጥርበት ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: አስመሳይ ድርጅቶችም ካሁኑ ፈንድቀዋል:: የተቃዋሚዎች ስብስብ የሚል ፉት ቢሉት ጭልጥ የሚል እድር ለመፍጠር እየተራሩጡ ስለመሆኑ የውስጥ አዋቂዎች ጠቁምዋል:: እድሩም "የሰለጠነ ፖለቲካ" መንገድ እየተከተለ ወያኔ በድል የሚደመድመውን ምርጫ ሊያጅቡ ተግቶ ይሰራል::

ስለመልካም ድጋፋቸው ምናልባት ከወያነ 5 ከበዛም 10 የፓርላማ ወንበር ያገኙ ይሆናል:: ካስሩ አራቱ ዶክተር ብርሃኑ፡ ብርቱኳን፡ ጽጌ፡ ካንጃው ደግሞ ወይ መርሻ አለያም ዶክተር ጌታቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ ከወዲሁ ይገመታል:: ዶክተሩ ምናልባት አሁን ካልጎመጁ በስተቀር ብዙ ጊዜ ሲደመጡ እንደሚሉት መለስ ስልጣን ሊሰጠኝ ጠይቆኛል:: ግን ብሄድ አሁን ከማገኘው ደሞዝ የበለጠ አይሆንም:: በማለት የራሳቸውን ምኞት በገንዘብ መጠን ገምግመው ላለመሄድ ወስነዋል:: እንግዲያውስ? ምናልባት መርሻ ሊሆን የሚችልበት አንድ ጥርጣሬ ይኖረኛል:: የኢሕአፓ ምልአተ- አባላት ድጋፍ ሲነፍጉት "ኢሕአፓን አጠፋዋለሁ" ብሎ መዛቱ ያደባባይ ሚስጢር ሁኗል:: በምድረ-ፈረንጅ በኢሕአፓ ላይ የከፈተው ጦር ድባቅ በመመታቱ ሃገር ቤት ገብቶ በወያኔና በመሰሎቹ እየተደገፍ ሌላ ጦር በኢሕአፓ ላይ ለመክፈት ሊገባ ይችል ይሆናል::

የፖለቲከኞቹ መንገድ አሳሳች ሆኗል:: በስመ ተቋሚ ጎራ ግሳንግሱ ሁሉ ተወሽቋል:: ወያኔን ሕጋዊ ለማድረግ ወገባቸው እስኪጎብጥ የሚሰሩ ተጎንባሽ ድርጅቶችም እንደአሸን መፍላቱ እየተስተዋለ ነው:: ድርጅት ሰባሪዎችና ከፋፋዮች ያለስጋት አንገታቸውን እቅንተዋል:: ሁሉንም ተጎንባሾች የሚያሰባስብ አካል ለመፍጠርም ከወራት በፊት ሽር ጉድ እያሉ ስለመኖሩ እማኝ መቁጠር አያሻም:: የስደት መንግስት ሰባኪዎች ባይሳካላቸውም ሙከራቸውን አሳይተውል:: ድርጅት አያስፈልግም ባይ ወኔ ሰላቢዎችም ላንቃቸው እስኪሰነጠቅ እየቧረቁ ነው:: ሃቀኛ ድርጅቶችን ለማጣጣል ከግራ ወደቀኝ ከላይ ወደታች በመወናጨፍ ላይ ያሉ አድር ባይ ግለሰቦችና መጤ ድርጅቶች የትግሉን አካሄድ ሲያምሱና ሲያሳምሱ እያየ ነው:: የትግሉ ጎዳን ድቅድቅ ጨለማ ተላብሷል:: የሚነጋ አይመስልም:: ሆኖም ግን ይህ የህዝብ ትግል ድልን መቀናጀት አይቀሬ ነው:: "**ሊነጋ ሲል ይጨልማል**" አይደል የሚለውስ አባባሉ!

ኢትዮጵያችን በቁርጥ ቀን ልጆቿ ነጻነታ ይከበራል!
ባንዳ ምሁራንና ባንዳ ደናቁርት በትግላችን ይኮላሻሉ!